# ተስፋን የዘራ  አውሮፓ አቀፍ ሰላማዊ ሰልፍ።

*ሥርጉተ ሥላሴ*
*መጋቢት 2001 ዓ.ም.*




ተሰፋ ... ብሩህ ራዕይ፣ ዓላማ፣ ግብ፣ ጉዞ፣ ሥርዕየት፣ ምህረት፣ ሀሴት ወዘተ ... ነው። በሌላ በኩል ተስፋ ኑሮ፣ህይወት፣ ቅዱስ መንፈስም ነው። ተስፋ የሌለው ጉዞ ሆነ ተስፋ የሌለው ዓላማ ሁል ጊዜ ጨለማ ነው። የተሰፋ መንገድ ምንጊዜም ብርሃናማ ነው። ተስፋ ያለው ጉዞ ሁሌም ውጤትን ሰንቆ፣ ትጥቅን አሟልቶ፣ ሀይልን አሰተባብሮ በፍጥነት ለመራመድ ቀና ነው።

ተሰፋ ጥሩ  የዓላማ መንገድ ጠራጊ መሀንዲስ ነው። መሀንዲስነቱ ገቨ፣ረ ውጤትም ነው። ተሰፋ ብቁ የሀይል ምንጭ አፍላቂ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ፍልቀቱ ጠቃሚ እና ገንቢም ነው። ተስፋ ረሀብን ማስታገስ ብቻ ሳይሆን ጠንካራ ካገኘ ሁሌ መና ቀላቢም ነው።

ተስፋ ለምለም፣ አዛኝ እና ሩህሩህም ነው። ርህራሄው ሆነ ደግነቱ ተሰፋ ላጡ ሀይሎች በመሆኑ በድርጊቱ ጥግ እና ጋሻ ነው። የተስፋ ማሳ ለተገፉ፣ ላለቀሱ፣ ባይታወር ለሆኑ ሁለ ፈውስ አደይነቱ በእኩልነት ነው። በተሰፋ ዙሪያ አንዱ ልጅ ፣ አንዱ እንጀራ ልጅ የለም። እንደ እናት ወይንም እንደ ፈጣሪ አምላክ የእኩልነት ዓውደ ምህረት ነው።

... 2




አዎን፣ በቅን ኢትዮጵያን አዘጋጅነት እና ትጉህ ተሳትፎ በታለቋ ብርቴን በለንደን የተካሄደው አውሮፓ አቀፍ ሰላማዊ ሰልፍ ለዘመኑ አዲስ የተሰፋ ፍሬን ያዘመራ፣ የፀረ- ወንበዴውን ጎራ የጥንካሬ እና የብርታት ልዩ ወኔ የፈጠረ ታሪካዊ ክንውን ነው።

‚አንድ ሀገር አንድ ሕዝብ’ ትውፊታችን፣ የእኛነታችን መግለጫ የሆነውን የባንዲራያችን ንፁህ ተፈጥሮ አመሳከሪ መሪ መርህ። የማንነታችን መውጫ መዝገብ፣ ሰነድ፣ መዘክር ነገረ-ሚስጢር። ነገር ግን የፋሽስቱን ጠ/ሚ ሄሮድስ መለስ ዜናዊን ህቅታ እና የጉሮሮ አጥንት የሆነው መራሂ የአብሮነት ህበረ ዜማችን ልደቱን  በብርታኒያ በታላቅ ሥርዓት ነበር ያከበረው።

ከሁሉ በላይ ሊያስደስት የሚገባው አክሊል ጉዳይ የለንደኑ ሰላማዊ ሰለፍ ወንበዴ እንዳሰበው ... ኢትዮጵያ ከልጆቿ ጋራ መሆንዋ በስማ በለው ሳይሆን ጠ/ሚ ሄሮድስ ዜናዊ በብሌናቸው እንዲመለከቱ ጊዜ እና አጋጣሚ በራሱ ፈረደ። ተመስገን እንኳን ለዚህ አበቃን። የነበረባቸውን የምጥ ሰዓትም እኛንም አሳየን መኖር ደጉ ... ጊዜ ባለ ሚዛኑ እንደሳቸው ገምድል አይደለም እና።

በዕውነት አቶ መለስ ከሰሩ። እንዳሰቡት እሳቸው በነሰነሱት የጎሰኝነት መረዝ ኢትዮጵያውያን ተጠቂ አለሆኑም። በአንድ ቅዱስ ኢትዮጵያዊ መንፈስ እንደ ጥንቱ እንደ ጥዋቱ በእምዬ እቅፍ ውስጥ የሁላችን ህሊና እና ልብ የወከሉ ከአንድ ሺህ በላይ ህይወቶቻችን ድምፃችንን አንደበታችን ሆነው አሰሙ።

…3

ተዋህድን፣ ተቀራርብን፣ ተዛዝነን፣ ተፋቅረን የመኖራችን የ3000 ዘመናት ታሪክን ተስፋዎቻችን - ተስፋችንን - በፍፁም ተሰፋ አዘመሩት። ዜማዊ እና ቅኔአዊ የሆነው የ80 ብሄረሰቦች የመቻቻል እና የጋራ አንባ በአንድነት ሸማ ለንድን ላይ ዳግም አበበ። አበራ፣ ደመቀ፣ በልዩ ፍቅር ተሽሞነሞነ ...

የወንበዴው መንግስት መሪም ቅስም ተሰበረ፣ የወንበዴው ድርጅት የተሰፋ አከርካሪው ደቀቀ። የመኖር ራዕዩ ደመነበት። እንቅስቃሴውም ደመ ነፈስ ሆነ፣ የተነሳበት ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊነት አሽዋ ውስጥ የመቅበር ህለሙ እንጦርጦስ ወረደ። ዲሞክራሲ እያለ የሚያላግጠው፣ ሆነ የሚያላዝነው ጉሪያው በዓለም ሕዝብ ዘንድ መለመላውን ተገተሮ ማጣፍያው አጠረበት፣ ውይ ለወንበዴው ቀን ቀኑን ነሳው። ተመስገን!!!

ከእንግዲህ በኋላ እያምታቱ በለበጣ መዘመን ፈፅሞ የማይቻል ነው። ከመቼውም ጊዜ በላይ የለንደኑ ሰላማዊ ሰለፍ የወንበዴውን መንግሰት መሪ እና ዓላማ ውልቅልቁን አውጥቶታል እና።




*<u>... ዒላማው እንዲህ ከታሰበው ደርሶ ጠላትን ሲያብረከርክ፣ ሲደረምስ፣ ሲያርበተብት፣ ተኳሽ እና ምላጭ ከዒላማ ጋር ለኪዳን ሲበቁ ድሉን እጥፍ ድርብ ያደርገዋል። ወንዳታ! ፍፁም የሆነ የአርበኝነት ውሎው በመጠነ ሰፊ ድል ተቋጨ። ተስፋን ፈጥሮ፣ተስፋን ዘርቶ፣ ተስፋን ያዘመረ ገድል!</u>*

አሁን ሆዳችን በተሰፋ ተሞልቷል። *በሌላ በኩል ደግሞ ተስፋን ተስፋ ማድረግ የሚቻለው ለተሰፋው ሁልጊዜ መሪ ሲኖረው ነው። የተስፋችን መሪ ደግሞ ድርጊት ነው። ተሰፋ የመምጣቱን ያህል ሲያስፈልገው ደግሞ ተስፋ ለሽ ብሎ ይተኛል በቂ ስንቅ ካለገኘ፣ ... እሱም ተግቶ በተግባር ቀድሞ በመገኘት ለወንበዴው መንግሰት የጥቃት እንቆቆን ወይንም አሳንገላን አስገድድዶ መጋት።*

...4




… ተከታታይ የፖለቲካ ሥራዎችን መፈፀም፣ ድህረ ገፆችን ሆነ ሀገር የሚደርሱ ሚዲያዎችን ማጠናከር፣ ፀረ ወንበዴ ትግሉን በብቃት እና በፅናት በመምራት ላይ የሚመሩትን እንደ አንድነት ፣ ግንቦት 7 ባሉ ድርጅቶች የበቃ ተሳተፎ በማድረግ ሳያወላውሉ ከጎናቸው መቆም፣ የወንበዴን ዕድሜ ያሳጥረዋል። የማከብራችሁ ወገኖቼ የድሉ ገነት በመዳፋችን ነው። ከጠነከርን እና ሁለገብ ተሳትፎአችን ካሳደግን።
… እርስበርሳችን በመደማመጥ እና በመከባበር በትግሉ ማዕቀፍ ወስጥ በመሆን ከቆረጥን እና ከፀናን ምንም የሚሳነን ነገር የለም ሁሉ አለን።

በሌላ በኩል ደግሞ ፀረ ወንበዴ ትግሉን ውስጥ ለውስጥ በመሸርሸር ዕምቅ ፍላጎታቸውን የሚፈፅሙትን ደፍሮ ማጋለጡን ሥራዬ ብለን ልንይዘው የሚገባ ጉዳይም ነው። ሁላችንም የአጠቂ ሠራዊት አባልተኝነታችን በድርጊት በማስጌጥ፣ የደህንነት ሠራተኛ መሆን አለብን። ስለሆነም ወቅቱ ከጠየቀው የትግል ስልት ጋር አብርን በመጓዝ ፀረ-ወንበዴ ትግሉን ከመከላከል ወደ ማጥቃት ማሸጋገር ትውልዳዊ ግዴታችን ነው።

እንዲሁም ወንበዴውን ሰላም በሚያሳጡ ጉዳዮች ላይ ነቅተን መሳተፍ፣ ከተግባር ጋር ማዋዋል እና መዋል ማደር፣ የተግባር ዕድምተኛ ለመሆን መቁረጥ፣ ለራሳችን ህሊና የሚያሳርፍ እርምጃዎች ላይ መትጋት ይኖርብናል። ምንጊዜም የምናጠፋው ጊዜ ሆነ የምንከፍለው መስዋትነት ፀረ-ወንበዴ ትግሉን አትራፊ እና ተጠቃሚ በሚያደርጉ ጉዳዮች ዙሪያ ብቻ መሆን አለበት።

የተከበረ ተግባራትን የፈፀሙትን የለንደን ሰላማዊ ሰለፍ  ዕደምኞች ድካም ተጋሪነታችን የሚረጋገጠውም … እኛ ደግሞ ማድረግ በሚገቡን ክስተቶች ሁሉ ሆነን መገኘት ስንችል ብቻ ነው። የዜግነት በርትህ እጦት ታፍኖ ላለው 80 ሚሊዮን ሕዝብ የተስፋው መጠለያ መሆን መቻል በራሱ የፅደቅ ትሩፋት የሚያሰጥ … ሲታደሉት ብቻም የሚገኝ ይመስለኛል።



እነዛ ማንኛውም ችግር ሳይበግራቸው ከተለያዩ የአውሮፓ ሀገሮች የተሰባሰቡ  ለንደን ላይ አባሪ እና መሪ ድርጊት የከወኑ የተግባር ጀግኖችን ድካም ውለታ ከፋይነታችን የሚረጋገጠው ተሰፋን ዘርቶ ያመረተውን ብርቱ ገበሬ ፈለግ በተግባር ስንከተል ብቻ ነው። በሰተቀር ተሰፋ አንዳንድ ጊዜ ሾላካ ነው እና እንዳይሾልክብን ቀበቶን እና መቀነትን ጠበቅ ነዋ!

## *ዕልፍ ነን እና ዕልፍነታችን ዕልፍ እናድርገው።*

## *ትውልዳዊ ድርሻችን በህብረት እንወጣ!!*

